ሳምንታዊ ዜና (ግንቦት 30 ቀን 2000 ዓ. ም.)

የኑሮ ውድነት አስከፊ ደረጃ ላይ መድረሱ አሳሳቢ ሆኗል፣ ህዝቡ እየተራበ ወያኔ ለሹማምንቱ ድግስ ብዙ ሚሊዮን ብር እያወጣ ነው፣ በሀገሪቱ የረሃብተኛው ቁጥር ጨምሯል፣ ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች የሚሰጡት የእርዳታ እህል በወያኔ ሹማምንት እየተቸበቸበ መሆኑ ተጋለጠ፣ ወደ ሱማሌ ክልል የተላከው የእርዳታ እህል መንገድ ላይ ቀረ፣ ሕወሓት እና ብአዴን ምን እየሆኑ ነው? ምስራቅ ወለጋ ውስጥ ወያኔ በተኮሰው ተንኮል ከ140 ሰው በላይ ሞቶ፣ በብዙ ሺህ የሚሆን ተፈናቅሎ የ85ቱ ዓመት መቶ አለቃ ግርማ ምንም አልተፈጠረ ብለው ሸመጠጡ፣ ኢንጅነር ኃይሉ ሻወል ደማቅ አቀባበል ተደረገላቸው፣ የወያኔ የደህንነት ክትትልም ቀጥሏል»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»

ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ ሌላም ዜና በዝርዝር ንብቡ
…………………………………………………………

በሀገሪቱ የተከሰተው የኑሮ ውድነት ከዕለት ወደ ዕለት እየከፋ መምጣቱ በመላ ሀገሪቱ ዜጎች ዘንድ ድንጋጤን እየፈጠረ መሆኑ ተነገረ::

ቀድሞም ወያኔ በዘረጋው ዘረኛና ጎጠኛ ፖሊሲ ምክንያት ኑሮ ያደቀቀው የሀገሪቱ ሕዝብ አሁን ደግሞ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ የኑሮ ውድነቱ ማሻቀቡ እጅግ አስደንጋጭ መሆኑ ታውቋል::

ሰሞኑን ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ተዘዋውሮ እንደተመለከተው ከሆነ የአንድ ኩንታል ጤፍ ዋጋ ከ1100 እስከ 1200 ብር እየተሸጠ ሲሆን፣ በሌሎችም ጥራጥሬና ፍራፍሬዎችም ላይ በሀገሪቱ ታሪክ ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ ዋጋው ማሻቀቡ የሀገሪቱን ሕዝብ ከማስደንገጡም በላይ በቀን አንድ ጊዜ እንኳዋን ለመቅመስ አስቸጋሪ ደረጃ ላይ መደረሱን ከነጋዴዎችና ከህብረተሰቡ ያገኘውን ጥቆማ ዋቢ አድርጐ ዘግቧል::

የአንድ ኪሎ ሙዝ ዋጋ ከ4.50 እስከ 5 ብር ፤ አንድ ኪሎ ቡርቱካን ከ8ብር እስከ 9ብር እየተሸጠ ሲሆን በመጠነኛ ዋጋ ይለያይ እንጂ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ተመሳሳይ መሆኑን የጠቆሙት ነጋዴዎች በአሁን ሰዓት ለንግዱም ሕብረተሰብ ምንም ምቹ ሁኔታ እንደሌለ እና የችግሩም ተካፋይ እንደሆኑ ገልፀዋል ሲል ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን አስረድቷል::

የኑሮ ውድነቱ ሕዝቡን ከድህነት ወለል በታች ያደረገው ከመሆኑም በተጨማሪ በመኖርና ባለመኖር መሀከል እንዲሆን ያስገደደው ሲሆን ጉጠኛው ወያኔ ግን በአንፃሩ ለግለገል ካድሬ ባለሥልጣናት ሳይቀር በየመስሪያ ቤቱ ጤፍ በርካሽ ዋጋ እያከፋፈለ መሆኑ አሳዛኝና አሳፋሪ ነው ያሉት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በዚህ

አኩሁዋን ለ3 ወራት ከቀጠለ እጅግ አስደንጋጭ ክስተት ሊፈጠር ይችላል ሲሉም ያላቸውን ስጋት ይገልፃሉ።

ወያኔ ለካድሬዎቹና ለሹማምንቶቹ በድብቅ ካስቀመጠው መጋዘንና በየገጠሩ ተዘዋውሮ የገዛውን ጤፍ እያመጣ በርካሽ ዋጋ ከማደሉም በተጨማሪ በተገኘው አጋጣሚ ግብዣ እየጠራ እያዝናናቸው እንደሚገኝ የጠቆሙት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ሕዝቡ በርሀብና በስቃይ ውስጥ መኖሩ እየታወቀ ሰሞኑን የግንቦት 20 ተብሎ በሚከበረው በዓላቸው ምክንያት ለድግስ ተብሎ የሚወጣው ወጪ እጅ ከፍተኛ እንደሆነ አብራርተው ወያኔ ለሕዝቡ ወትሮም ቢሆን የማይጨነቅና የማያስብ በመሆኑ የተነሳ አንዳችም የዋጋ ማረጋጋት ስራ ያልሰራ መሆኑ ያበሳጫል ሲሉም በንዴትና በእልህ ይገልፃሉ።

አንዳንድ ቤተሰብ ውስጥ በቀን አንድ ጊዜ መብላት ተስኗቸው ምግብ በፈረቃ እንዲያገኙ የተገደዱበት ደረጃ የተደረሰ መሆኑን የጠቆሙት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በደርግም ሆነ በሀይለስላሴም ችግሮች ተከስተው ነበር። የአሁኑ የወያኔው ግን በሀገሪቷ ታሪክ በፍፁም ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ እጅግ የኑሮ ውድነቱ አሻቅቦ ሕዝቡ በከፍተኛ ችግር ውስጥ እንዲወድቅ ሆን ብሎ እየሰራ ይገኛል ሲሉ እንባ እየተናነቃቸው ይገልፃሉ።

ወያኔ ሕዝቡን በድህነት አንገቱን እንዲደፋ ለማድረግ አስቦ ለከፍተኛ የኑሮ ውድነት እየዳረገ መሆኑን የገለፁት አንድ የአዲስ አበባ ነዋሪ የሚገርመው ለወትሮው አንደኛው ቢቸገር ሌላኛው ኖሮት ይረዳ ነበር። ዛሬ ግን ሁሉም የዕለት ጉርስ ለመሸፈን እጅግ በጣም የተቸገረበት ደረጃ ላይ መድረሱን እያየ ለካድሬዎቹና ለሆድ አደር ሹማመንቱ በየቀኑ በመቶ ሺህዎች የሚቆጠር ብር ወጪ እያደረገ በግብዣ እያንበሻበሻቸው መገኘቱ አሳፋሪና ወራዳ ተግባር ነው ያሉት እኚሁ አዛውንት ወደፊት ምን ሊመጣ እንደሚችል መገመቱ እጅግ ይከብዳል ብለዋል።

በአሁን ሰዓት በመላ ሀገሪቱ ከ6 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ረሀብተኛ እንዳለ የአለም አቀፉ የምግብ ድርጅት ገልጾ ይህ አሀዝ እያሻቀበ እየሄደ ስለሆነ አስቸኳዋይ መፍትሄ ይሰጠው በማለት እየወተወተ ባለበት ወቅት የወያኔ አምባገነን ቡድን ግን የሕዝቡ መራብና መጠማት ምንም ሳይመስለው ይልቁንም ሀገሪቷ ውስጥ አንዳችም ችግር ያልተከሰተ ለማስመሰል ዝም ከማለቱም በላይ ሰሞኑን የማስታወቂያ ሚኒስቲር

መስሪያ ቤት በአለም አቀፍ ድርጅቶች ላይ ለምን ገመናዬን አጋለጣችሁ በሚል አሳፋሪ መግለጫ መስጠቱ ታውቁዋል::

«ሀገሪቱ እያስመዘገበች ያለው እድገት ያስቀናቸው አለምአቀፍ ድርጅቶች ነን ባዮች በዜጎቻችን ስም እርዳታ እየሰበሰቡ መሆናቸው የእኛን ጥሩ ገጽታ ለማጉደፍ ነው» ሲል መግለጹ መላውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ያስቆጣና ያበሳጨ ሲሆን ፤የአለም አቀፍ ድርጅት ሰራተኞችን ደግሞ ያሳዘነ መሆኑ ታውቁዋል::

የሀገሪቱ ዜጎች በርሀብ እንደ ቅጠል እየረገፉ ባለበት በዚህ ወቅት የአለም አቀፉን የምግብ ድርጅት ለምን ለተራቡት ዜጎች እርዳታ አቀረባችሁ፤ሕዝቡ መራቡንስ ለምን ለአለም ህብረተሰብ አጋለጣችሁኝ በማለት የደነፋውና እብሪት የወጠረው የወያኔ ቡድን በድንጋጤ በሰጠው መግለጫ ተቀማጭነታቸው አዲስ አበባ የሆኑ ዲፕሎማቶችን ሳይቀር ያስገረመና ያስደመመ መሆኑ ታውቁዋል::

በአሁን ወቅት በአርሲ ውስጥ ከ50 በላይ ሕፃናት በምግብ እጦት የሞቱ ሲሆን በሌሎቹም የሀገሪቷ ክፍሎች በተመሳሳይ በምግብ እጥረት የተነሳ በርካታ ሰዎች እየሞቱ መሆኑ ከተለያዩ አካባቢዎች የሚወጡ ዘገባዎች ሲያስረዱ ወያኔ ገመናዬ ወጣ ብሎ ለጋሽ ድርጅቶችን መሳደቡ አስገራሚ እንደሆነባቸው ለዲፕሎማቶች ቅርበት ያላቸው ወገኖች ሲገልጹ ተደምጠዋል::

ግፈኛውና አምባገነኑ ወያኔ አለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች በሀገሪቷ ክፍሎች ተዘዋውረው እርዳታ እንዳይሰጡ ከተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ወግናችኋል እያለ ሰበብ እየፈጠረ ከማባረሩ በተጨማሪ ለረሀብተኞች እንዲሰጥ የተላከውን ስንዴ እየቸበቸበ ለካድሬዎቹ መዝናኛ እያደረገው እንደሚገኝም ታውቋል::

በየቀኑ ዜጐች በረሀብ እንደቅጠል እየረገፉ ባለበት በዚህ ወቅት አስቸኩዋይ የአደጋ ጊዜ ጥሪ ካለማድረጉም በላይ ለጋሽ ድርጅቶች ለረሀብተኛ ዜጐች ድጋፍ እንዳያደርጉ ሰበብ እየፈጠረ ከማስቀረቱም በላይ የእርዳታ እህሉን ወደ ወታደራ መጋዘን እያጓጓዘ መሆኑም ምንጮች ጨምረው ገልፀዋል::

ሰሞኑን ወደ ምስራቅ ኢትዮጵያ ሱማሌ ክልል በጐርፍና በረሀብ ለተጐዱት ዜጐች አንድ የአለምአቀፍ ድርጅት የእህል እርዳታ ለማድረግ በማጓጓዝ ላይ እንዳለ

በአካባቢው የታጠቁ ኃይሎች ስላሉ ችግር ይፈጠራል በመሆኑም ሌላ ቦታ ይራገፍ በማለት የወያኔ ባለስልጣናት በመከልከላቸው ለሕዝቡ ሳይደርስ ቀርቶ እህሉ እየተቸበቸበ መሆኑን ምንጮች ጠቁመው ወያኔ መላ የሀገሪቷን ሕዝብ በረሀብና በችግር እየቆላ እንደልቡ ሊኖር ካለው ሕልም የተነሳ የተለያዩ ደባዎች በሕዝቡ ላይ እየፈፀመ መገኘቱንም ምንጮች ያስረዳሉ።

ግንቦት 20 በዓሌ ነው እያለ ሽብ ረብ በማለት ላይ የሚገኘው የወያኔ ቡድን በየቀኑ ለድግስ እጅግ መጠኑ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ በማባከን ላይ መሆኑ የሚያሳዝን እና የሚያሳፍር ነው ያሉት አንድ አዛውንት ይህንን ግፍና መከራ እንድንጋት እያደረጉን ያሉትን ሹማምንት የኢትዮጵያ አምላክ ይፋረዳቸው ሲሉ እንባ እየተናነቃቸው ሲገልፁ ተደምጠዋል።

በአሁን ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ርሀብተኛ ዜጎች በመኖራቸው የተነሳ አለም አቀፍ ድርጅቶች እንኩዋን አቅማቸው የፈቀደውን ለማድረግ እንዳይችሉ ወያኔ ከፍተኛ ደባ እየሰራ መሆኑንም ከደረሱን ጥቆማዎች ለማወቅ ተችሉዋል።

በሌላ በኩል የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ከ3 ዓመት በኋላ በእርግጠኝነት ስልጣኔን እለቃለሁ በማለቱ የተነሳ በወያኔ ሹማመንት ዘንድ ከፍተኛ ተቃውሞ ማስነሳቱን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ጥቆማ ገለፀ።

እንደ ምንጮቹ ጥቆማ ከሆነ መለስ ዜናዊ ባለፈው ሳምንት የኤርትራ ተቃዋሚዎች ሚዲያ ለተባለው በሰጠው ቃለ ምልልስ ላይ «በእርግጠኝነት ስልጣኔን እለቃለሁ። ከ3 ዓመት በኋላ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር እያልክ ትጠራኛለህ»በማለት በሰጠው ማብራሪያ ዙሪያ የወያኔ ሹማምንት በተለይም በረሀ አመጣሾቹ እንደተበሳጩና እንደተናደዱ ምንጮች ገልፀዋል።

በተለይም በአሁን ሰዓት በእኛ ላይ የፖለቲካ ኪሣራና የኢኮኖሚ ውድቀት ውስጥ እያለን ይህንን መናገርህ እጅግ አስደንጋጭ ነው በማለት በአቦይ ስብሀት አማካኝነት የተቆጡት ወያኔዎች ከዚህ ቀደምም ቢሆን ተመሳሳይ መግለጫ ሰጥተህ እንድታርም አድርገንህ ነበር አሁን ደግሞ ያንኑ መድገምህ ተገቢ አይደለም የሚል መልዕክት ማስተላለፋቸው ታውቋል።

በአቦይ ስብሀት በኩል የተነገረው መለስ እንዳለፈው ጊዜ ሁሉ እኔ እለቃለሁ አልኩኝ እንጂ ፓርቲዬ ትሰራለህ ካለ እቀጥላለሁ ብሎ ማስተባበያ እንዲሰጥ ቢጠየቅም ፈቃደኛ ሳይሆን በመቅረቱ መብሸቃቸውንም ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል፡፡

በተያያዘ የወያኔ ቡድን ግንቦት 20 በዓልን በሚያከብርበት እለት ድሉን ያገኘ ው ሕወሓት ብቻውን እንደሆነ እየለፈፈ መገኘቱ በብአዴን ካድሬዎች ዘንድ ቅሬታ ማስከተሉ ታወቀ፡፡

የሕወሓት ጄኔራሎች በሙሉ ስላሳለፉት ውጊያ እየፎከሩና እያቅራሩ ብቻቸውን ድል አድርገው እንደመጡ እየሰበኩ ባለበት ወቅት የብአዴን ካድሬዎች የኢትዮጵያን ፖለቲካ እንቅስቃሴ የጠነሰሰው ኢህአፓ መሆኑ እየታወቀ ስሙም አንዴ አለመጠቀሱ ያበሳጫቸው መሆኑንም የተገኘው ዘገባ ያስረዳል፡፡
በዚህም ምክንያት በኢትዮጵያ ቀደምት የሆነው የፖለቲካ ተቋም ኢህአፓ አንደነበረና እነሱም ከሱው ወጥተው ኢህዴንን እንደመሠረቱ በኋላም ብአዴን ብለው እንደቀየሩት በመግለፅ እነ ታደሰ ጥንቅሹ መግለጫ ቢሰጡም የኢህአፓ ስም መነሳት ያስፈራቸው ወያኔዎች የብአዴን ካድሬዎች የሰጡትን ቃለምልልስ ቆርጠው ማስቀረታቸውንም ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በአሁን ሰዓት በብአዴንና በሕወሓት መካከል መጠነኛ የሚባል ክፍተት መፍጠሩን ያስታወቀው የደረሰን ዘገባ በቅርቡም በጐንደር ወያኔ በፈጠረው ችግር ምክንያት ሕዝቡን ለማረጋጋት በሚል አዲሱ ለገሰ ወደ ስፍራው ቢሄድም አብሮት ጄኔራል ሳሞራ የኑስ እንደተጓዘና በተመሳሳይ በጅጅጋ የጉርፍ አደጋ በደረሰ ወቅትም ወደ ጅጅጋ ሲሄድ አባይ ፀሀዬ አብሮት እንደሄደ የጠቆመው ዘገባ በአሁን ሰዓት ወያኔዎች እርስ በእርስ በተለይም ህወሃትና ብአዴኖች እየተጠባበቁ መሆኑን ያሳያል ሲል ዘገባው ይገልፃል፡፡

ለ9 ወራት ከሀገር ውጭ የቆዩት ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ቅዳሜ ግንቦት 23ቀን 2000 ዓ.ም ወደ ሀገራቸው መመለሳቸው ታወቀ፡፡

ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ወደ ሀገራቸው በተመለሱበት ወቅት የፓርቲያቸው አመራሮችና ደጋፊዎች እንዲሁም ቤተሰቦቻቸው ደማቅ አቀባበል ያደረጉላቸው ሲሆን ሰኞ ዕለት ግንቦት 25 ቀን 2000 ዓ.ም. ደግሞ ቸርቸር ጉዳና በሚገኘው በቅንጅት ጽ/ቤት ውስጥ ደማቅ አቀባበልና የሪሴፕሽን ግብዣ እንደተደረገላቸው ታውቋል፡፡

ለ9ወራት በሕክምና፣ደጋፊዎችን በማደራጀት፣ አሜሪካ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ማብራሪያ በመስጠትና በመሳሰሉት ስራ ላይ የቆዩት ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ቅዳሜ ወደ ሀገር ቤት ገብተው ሰኞ ስራ የጀመሩ ሲሆን፣ ሐሙስ እለት ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ጋዜጠኞች መግለጫ መስጠታቸው ታውቋል።

የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ድርጅት ሊቀመንበር ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ወደ ሀገር ውስጥ ከገቡበት ዕለት ጀምሮ የወያኔው ቡድን በርካታ ቁጥር ያላቸው ደህንነቶችን አሰማርቶ በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ሳይቀር በሰላም መመለሳቸውን ሊጠይቅ ገብቶ የሚወጣውን ማንነት እየተከታተሉ እንዳሉና በቢሮዋቸውም አካባቢ ተመሳሳይ ስራ እየሰሩ መሆናቸውንም ምንጮች በተለይ ለፍኖተ ዲሞክራሲ ራዲዮ ገልፀዋል።

ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ከአሜሪካ ከመነሳታቸው አስቀድሞ ከፍኖተ ዲሞክረሲ ራዲዮ ጋር አጭር ቃለ ምልልስ አድርገው የነበረ መሆኑ አይዘነጋም።

በቅርቡ በምስራቅ ወለጋ ሲሳጋ ወረዳ ውስጥ ወያኔ በፈጠረው ተንኮል ምክንያት የሚኞች ቁጥር 140 ሲደርስ በርካታ ቁስለኞችና በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ስደተኞች በነቀምት እያሉ የሀገሪቱ ርዕሰ ብሔር ናቸው የተባሉት መቶ አለቃ ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ ምንም ግጭት አልተፈጠረም የተፈጠረው በእረኞች መካከል ድሮም ነበር አሁንም ያለ ነው ሲሉ መግለፃቸው ህዝቡን እያስቆጣ መሆኑ ታወቀ ።

ግንቦት 9 ቀን 2000 ዓ.ም የወያኔ ማፊያ ቡድን በተደራጀና በታጠቀ ኃይል የአካባቢውን ህዝብ ለተቃዋሚ ታጣቂዎች ያድራል በሚል ቀድሞም በጥቁር መዝገብ ውስጥ አስገብቶት የነበረው ወያኔ በወሰደው አረመኔያዊ እርምጃ ዜጐች በየጥሻው ወድቀው እንዲቀሩ የተደረገበት ሲሆን፣ አደጋውን ያደረሱት እርስ በእርስ በተፈጠረ ግጭት ነው ብሎ መግለጫ የሰጠ ቢሆንም መቶ አለቃ ግርማ ግን በ85 ዓመታቸው ምንም አልተፈጠረም ብለው መዋሸታቸው ህዝቡን እንዳሳዘነ ታውቋል።

ከግንቦት 9 ቀን ጀምሮ በጉሙዝ፣ በማሻና በሳሲጋ ወረዳ ውስጥ የመንግስት ስራ ሙሉ በሙሉ የቆመና የአካባቢው ተወላጆች፣ የመንግስትና የድርጅት ሠራተኞች እየለቀቁ በመውጣት ላይ መሆናቸው እየተገለፀ ባለበት ወቅት አንድም ሠራተኛ አልለቀቀም ሀገራችን በእድገት ጐዳና ላይ ትገኛለች ያሉት ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ

ከቪኦኤ ሬዲዮ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ላይ ሲሆን፣ እሳቸው ችግር የለም ባሉበት ዕለት እንኩዋን መንገዱ ተዘግቶ ትራንስፖርት መቋረጡ እየታወቀ በሽምግልና እድሜያቸው ይህንን የመሰለ ውሸት መግለፃቸወ በጣም የሚያሳዝን መሆኑን ቃለ ምልልሱን ያደመጡ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ማዘናቸውን ገልፀዋል።

በአሁን ሰዓት ቁስለኞችና ስደተኞች በነቀምት ሆስፒታል ውስጥ ያሉ ሲሆን፣ ለተሰደዱት ዜጐች አንዳችም የምግብና የመጠለያ እርዳታ ያልተደረገላቸው ከመሆኑም በላይ ለምን መጣችሁ አካባቢው ሠላም ነው በማለት የወያኔ ካድሬዎች እያዋከቡዋቸው መሆኑን ከነቀምት የደረሰን ዘገባ ያስረዳል።

ግንቦት 9 ቀን የተከሰተው ይኸው የወያኔ ማፊያ አመጣሽ ችግር እስከ ዛሬ ድረስ ምንም መፍትሄ ሳይጠሰው አካባቢው አሁንም በውጥረት ላይ መሆኑን የገለፀው ከነቀምት የደረሰን ዘገባ የወያኔ ቡድን እራሱ የፈፀመው አረመኔያዊ ተግባር በመሆኑ ወደ አካባቢው ፈጥኖም ካለመድረሱም በላይ የደረሰውን እልቂትም አለመግለፁ ያናደዳቸው የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኦሮሞ ተማሪዎች ከፍተኛ ተቃውሞ ማሰማታቸው ታውቋል።

ወጣቱና ተማሪው አንድ ላይ ሆኖ ጥያቄውን ማንሳት እንዳይችል በመንደርና በጐጥ ከፋፍሎ ያለው ወያኔ በወለጋ በፈፀመው አረመኔያዊ ተግባር የተበሳጩት የዩኒቨርስቲው የኦሮሞ ተማሪዎች ስለሁኔታው ማብራሪያ እንዲሰጣቸው የተለያዩ ሚኒስቴር መ/ቤት ኃላፊዎችን ለማነጋገር ቢሞክሩም ከንቀት ሌላ ምንም መፍትሄ ያላገኙ ቢሆንም ግንቦት 23 ቀን 2000 ዓ.ም ችግሩ ከተከሰተ 14 ቀን በኋላ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነር ወርቅነህ ገበየሁ እንዳነጋገራቸውና ሁለተኛም እንዲህ ያለ ድርጊት እንደማይፈፀም ቃል የገባላቸው መሆኑን የገለፁት ተማሪዎቹ እስከዛሬ ድረስም ምንም አይነት እርምጃ ያልተወሰደ በመሆኑ እየተበሳጩ መሆኑን ገልፀዋል።

እነዚህ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኦሮሞ ተማሪዎች ድርጊቱን የፈፀመው ማን እንደሆነ ገለልተኛ አካል ተቋቁሞ ጉዳዩ ተጣርቶ ለህዝቡ ይፋ እንዲደረግ ጭምር ጥያቄ አቅርበው የነበረ ቢሆንም ምንም ምላሽ ያጡት ተማሪዎቹ ሕዝባችን በእንዲህ ያለ ሁኔታ ውስጥ እያለ ምንም መማር ስለማንችል ላልተወሰነ ጊዜ ትምህርታችንን እናቋርጣለን በማለት ሲገልፁ መደመጣቸውንም ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል።

ወያኔ እራሱ ባዘጋጀውና በፈፀመው ወንጀል ጣቱን ወደ ሌላ መቀሰር ልማዱ በመሆኑ አሁንም ችግሩን ያስከተሉት የጉሙዝ ወረዳ ባለሥልጣናት ናቸው በማለት ብዙ የራሱን ካድሬዎች በአሶሳ እስር ቤት የከተታቸው መሆኑን ከአሶሳ የደረሰን ዘገባ ገልጿል።
ከግንቦት 16 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ለስብሰባ ትፈለጋላችሁ በማለት ወደ አሶሳ ካስጠራቸው በኋላ የወረዳውን ካቢኔዎች በሙሉ ለእስር የደረጋቸው ሲሆን በኦሮሚያም በኩል የሳሲጋ ወረዳ ካድሬዎች ላይ ተመሳሳይ እርምጃ ሊወስድ ይችላል በሚል አንዳንዶቹ ባለሥልጣናት አካባቢውን ለቀው እየወጡ መሆኑን ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በጋምቤላ፣ በጐንደር እና ወለጋ የታጠቁ ተቃዋሚ ኃይል ይገኝበታል ተብሎ በወያኔ ቡድን ከፍተኛ ስጋት ያሳደረ በመሆኑ ሁኔታውን ለማቀዝቀዝና ለማረጋጋት አስቦ እራሱ ያደራጀው ቡድን ይህንን የመሰለ አረመኔያዊ ተግባር ከመፈፀሙም በላይ ለተጐጂዎቹ እርዳታ ያለማድረጉ አሳዛኝ ነው ያሉት የሀገሪቱ ሕዝቦች በተለይም በረሀብና በእንግልት የተሰቃዩ ዜጐችን መልሶ ማሰቃየቱ የአውሬነቱ መገለጫ አንዱ ባህርይ ነው ሲሉም በንዴት ይገልፃሉ።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኦሮሞ ተማሪዎች ችግሩን ያደረሰው ማን እንደሆነ ይጣራ በማለት ያነሱት ጥያቄ ያስደነገጠው የወያኔ ቡድን የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ወርቅነህ ገበየሁን እንዲያነጋግራቸው ተደርጐ የተድበሰበሰ ምላሽ ከመስጠት ባለፈ የረባ ማብራሪያ ያልሰጣቸው መሆኑን የገለፁት ተማሪዎቹ ከድርጊቱ ጀርባ ማን እንዳለ የሚያሳይ ፍንጭ ያገኘን ይመስላል ሲሉም ጥርጣሬያቸውን ገልፀዋል።

ይህ እየሆነ ባለበት ሰዓት እንኩዋወን የሀገሪቱ ርዕሰ ብሔር ናቸው የተባሉት መቶ አለቃ ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ ከዕድሜያቸው ጋር ፍፁም ያልተመጣጠነ አይን ያወጣ ውሸት መዋሸታቸው አሳዛኝ ከመሆኑም በላይ አሳፋሪ ነው ያሉት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ምናልባትም ቃለ ምልልሱን ሲያደርጉ ከፊታቸው የሚያስፈራሩ ባለሥልጣናት ይኖሩ ይሆናል ስሉም ግምታቸውን ይሰነዝራሉ።

በአሁኑ ሰዓት በአካባቢው የመንግስትና የድርጅት ስራ የተቋረጠ ሲሆን መንገዱም ተዘግቶ በአካባቢው የቀሩ ዜጐች ለከፍተኛ ችግር ተጋልጠው ያሉ መሆኑንም ተማሪዎቹ እየገለፁ ይገኛሉ።

በሌላ ዜና እውቁ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሣሁን ግንቦት 27 ቀን 2000 ዓ.ም ፍርድ ቤት ቀርቦ እንደገና ከአንድ ወር በኋላ መቀጠሩ ታወቀ::

ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሣሁን በ1999 ዓ.ም ፊት ብር አካባቢ ሰው ገጭተሀ ገድለሀል በሚል በሐሰት ክስ ተመስርቶበት ዋስትና ተከልክሎ ቃሊቲ እስር ቤት ከገባ 55ኛ ቀኑን ያስቆጠረ ሲሆን፣ ሰኔ 27 ቀን 2000 ዓ.ም ሁለት ወሳኝ ጉዳዮች እንደሚታዩ አንዳንድ የሕግ ባለሙያዎች ገልፀዋል::

ይህንንም ሲያስረዱ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሣሁን አቃቤ ሕግ ያቀረበው ማስረጃ የተጠናከረ ከሆነ ክሱን ተከላከል የሚል ሲሆን፣ አቃቤ ሕግ ያቀረበው ማስረጃ አጥጋቢ ካልሆነ ውድቅ አድርጎት በነፃ ያሰናብተዋል ብለዋል::

አሁን እንደተከታተልነው ከሆነ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል እርስ በርሱ የተጋጨና የተጣረሰ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ውድቅ ሊያደርገው እንደሚችል የሳሳ ግምት የሚሰጡት የሕግ ባለሙያዎቹ በፊትም ቴዲን ለማጥቃት ሆን ተብሎ የተሸረበ ሴራ በመሆኑ እንጂ ክስ ሊመሰረትበት አይገባም ሲሉ ገልፀዋል::

ግንቦት 27 ቀን 2000 ዓ.ም ከጧቱ 12 ሰዓት ጀምሮ በሁለቱም የፍርድ ቤት መግቢያ በሮች ላይ ሠልፍ የነበረ ሲሆን፣ በተለይም ተሽከርካሪ ይዘው የመጡት ደጋፊና አድናቂዎቹ በመብዛ ቸው የተነሳ ከጦር ኃይሎች ወደ ልደታ የሚወስደው መንገድ ከኮካኮላ ማዞሪያ በኋላ ለሰዓታት ተዘግቶ እንደዋለም ለማየት ተችሏል::

ያለምንም ኃጢያቱ በወያኔ ቡድን በተቀነባበረ ሴራ የተከሰሰው
የቴዲ አፍሮን የፍርድ ቤት ውሎ ለመከታተል የተገኘው ሕዝብ ብዛት ያስደነገጣቸው ወያኔዎች በፌዴራል ፖሊሶች አማካኝነት ገና ወደ ፍርድ ቤት ሳይገባ ሕዝቡን እየበታተኑ የነበረ ቢሆንም በተለይ ወጣቱ ሲጋፈጣቸው ተስተውሏል::

በዕለቱ ችሎቱ የተሰየመው 4ኛ ምስክር ባለመገኘቱ ለጣቢያ የሰጠው የምስክርነት ቃሉ ተያይዞ ይቅረብ በሚል የነበረ ሲሆን፣ ይህንኑ ዓቃቤ ሕጉ አቅርቦ ብይን ለመስጠት አንድ ወር የተቀጠረ ሲሆን ሆን ብለው በተቀነባበረ ድራማ ያሰሩት ቴዲን ጉዳዩን ለማየት የአንድ ሳምንት ጊዜ ቢበቃም የወያኔው ካድሬ ዳኛ ልዑል

ገ/ማርያም ግን ለ1 ወር መቅጠሩ ያበሳጫቸው ጉዳዩን ሊከታተሉ ፍርድ ቤት የተገኙ ት አድናቂዎቹ በአብዛኛው በንዴትና በእልህ ሲያለቅሱ ለማየት ተችሏል።

ወያኔ ሊያጠቃው የሚፈልገውን ግለሰብም ሆነ ቡድን የተቀነባበረ ድራማ ሰርቶ እንደሚፈፅመው ሁሉ በቴዲ አፍሮ ላይም ተመሳሳይ የግፍ ድርጊቱን እየፈፀመ መሆኑ ግልፅ የወጣበት መሆኑንም እነዚሁ ዜጎች ይገልፃሉ።

በመጨረሻም በወያኔ ማፊያ ቡድን መሪ ስብሐት ነጋ የሚመራው ቡድን በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚፈለጉ ሰዎች ናቸው የተባሉትን እያሳፈነና እያስገደለ መሆኑን ከድህንነት ቢሮ ሾልኮ የደረሰን ጥቆማ ገለፀ።

ከግንቦት ወር መጀመሪያ ላይ የተጀመረው አፈናና ግድያ በየቀኑ ሁለትና ሶስት ሰዎች በየድልድዩ ውስጥ ተጥለው እየተገኙ ሲሆን፣ ሟቾቹ በሙሉ የወያኔን ቡድን የሚነቅፉ ተቃዋሚዎች እንደሆኑም ለማወቅ ተችሏል ሲል ይኸው ጥቆማ ያስረዳል።

በባምቢስ ድልድይ ውስጥ ሁለት አስክሬን በታየ ማግስት በሲኤምሲ አካባቢም በተመሳሳይ ሁኔታ መገኘቱን የገለፀው የደረሰን ዘገባ በሥርዓቱ ውስጥ አደጋ ያደርሳሉ በሚሏቸው ግለሰቦች ላይ በስብሃት ነጋ የሚመራው ማፊያ ቡድን እያነቀ ገደሎ ጉድጓድ ውስጥ መክተት የጀመረው አሁን ባይሆንም በአሁን ወቅት ግን በየቀኑ ተስፋፍቶ መቀጠሉ እጅግ አስጊ ደረጃ ላይ መድረሱን ያሳያል ሲሉ የደረሰን ጥቆማ ያስረዳል።

በተለይም በባምቢስና በኢምፔሪያል አካባቢ ወድቀው የተገኙት 3 አስከሬኖች የሟቾቹ አስክሬን ፊት እንዳይታይ በሻሽ ተሸፍነው የነበረ ሲሆን፣ እንደተሸፋፈነና ወደ ምኒልክ ሆስፒታል እንደገባም ጥቆማው አስረድቷል። በአሁን ሰዓት በድርጊቱ የሚሳተፉት በስብሃት የሚመራ ቡድን ሲሆን ምንም ርህራሄ በሌላቸው ግለሰቦች ፈፃሚነት የሚከናወን መሆኑንም ጥቆማው ያብራራል።

ከዚህ ቀደም በስብሀት የበላይ ተቆጣጣሪነት በነ ሰለሞን አስመላሽና በዘሪሁን ተሾመ ተዋናይነት የመንግስት ጉዳይን እናስፈፅማለን በሚል ከከፍተኛ በለሀብቶች ላይ የንዘብ ዝርፊያ ሲያከናውን እንደነበረ መዘባችን አይዘነጋም።